ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም

# የተግባርና የቃለ-መጠይቅ ፈተና ሂደት አፈጻጸም መመሪያ

## 1. መግቢያ

በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በወጣው የፌደራል የመንግስት ሰራተኞች የቅጥር አፈፃፀም መመሪያ ኅዳር 2000 ዓ.ም ላይ የቋሚ የኮንትራትና የጊዜያዊ ቅጥር አፈፃፀምን አስመልክቶ ስለማስታቂያ አወጣጥና አጠቃላይ በሆኑ የቅጥር ሂደት ጉዳዮች ላይ ከሚገልፀው ውጪ የቃለ-መጠይቅም ሆነ የተግባር ፈተና ሲሰጥ እንዴትና በምን መመዘኛዎች ሊሰጥ እንደሚገባው የሚገልፀው ነገር ባለመኖሩ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚከናወኑ የቅጥር ሂደቶች ላይ ወጥነት ያለው አሰራር እንዲኖር የሚያደርግ በመሆኑና የሚኒስቴር መ/ቤቱም ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎች በየተቋሙ እንዲዘጋጁ የሚጋብዝ ስለሆነ የተግባርና የቃለ-መጠይቅ ፈተናዎች ሲሰጡ የሚይዙት መመዘኛ ነጥቦችንና ወጥ የሆኑ ፎርማቶችን ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ ይህ የቅጥር ሂደት አፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

በመጀመሪያው ዙር ምደባ ያላገኙ የአስተዳደር ሰራተኞች በሁለተኛው ዙር በሚደረገው ምደባ ውስጥ ለመካተት የሚከተሉትን መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

1. በመጀመሪያ ዙር ምደባ ለውድድር ቀርበው፤ በተወዳደሩበት ስራ መደብ ላይ አጠቃላይ አማካይ ነጥባቸው ከ50% በላይ አምጥተውና በነጥብ ተበልጠው ያልተመደቡ ሰራተኞች በ2ኛው ዙር ለቦታው የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት ካሟሉና ብልጫ ካገኙ ምደባውን ሊያገኙ ይችላሉ፣ ነገር ግን አማካኝ ውጤታቸው ከ50% በታች የሆኑ ሰራተኞች በ2ኛው ዙር ምደባ ላይ አይካተቱም፣
2. የ2ኛው ዙር ምደባ በመጀመሪያው ዙር ምደባ ያገኙ ሰራተኞችን አያካትትም፣

3. አንድ ሰራተኛ በ2ኛው ዙር ምደባ ውስጥ ለመካተት በ3ቱም የዩኒቨርሲቲው ካምፓሶችና የምርምር ጣቢያዎች ባሉት ቀሪ ክፍት የስራ መደቦች ላይ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፣

4. በዚህ ምደባ ወቅት በቋሚነት ተቀጥረው እያገለገሉ የሚገኙ የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች በ16/04/2005 ዓ.ም በቁጥርሲ.ሰ.ሚ30/ጠ18/22/459 ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ስቪል ሰርቪሲ ሚኒስቴር በተላከልን የአፈፃፀም መመሪያ መሰረት ቅድሚያ ተሰጥቶአቸው ይመደባሉ፣

5. በ2ኛው ዙር ምደባ ወቅት በአንድ የስራ መደብ ላይ ከአንድ በላይ ተወዳዳሪዎች በሚኖሩበት ጊዜ እንዳስፈላጊነቱ ሰራተኞቹ ያላቸው የትምህርት ዝግጅት በምልመላና ምደባ መመሪያው ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ነጥብ እየተሰጠውና ወደ 50% እየተቀየረ ለማወዳደሪያነት እንዲያገለግል ይደረጋል እንዲሁም ሰራተኞች ያላቸው የስራ ልምድን በተመለከተ ለ1 ዓመት አገልግሎት ወይም የስራ ልምድ 1 ነጥብ የሚሰጥ ሲሆን ይህ የነጥብ አሰጣጥ እስከ 19 ዓመት በዚሁ ሁኔታ የሚቀጥል ሲሆን ከ20 ዓመት በላይ ግን ነጥባቸው ከ20 መብለጥ የለበትም፡፡ በመጨረሻም ለስራ ልምድ የተሰጠው ነጥብ ወደ 50% እየተቀየረ ለማወዳደሪያነት እንዲያገለግል ይደረጋል፡፡

6. ሴቶችና የአካል ጉዳተኞች በስራ ልምድና በትምህርት ደረጃ በተሰጠው አጠቃላይ ነጥብ ከወንዶች ጋር እኩል ቢሆኑ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፣

7. በ2ኛው ዙር ለሚከናወኑ ምደባዎች ቅሬታ አይቀርብባቸውም፣

8. የምልመላና ምደባ ኮሚቴው የምደባውን ሂደትና የምደባውን ውጤት በተመለከተ ለበላይ አመራር አካላት በማቅረብ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡

9. በ2ኛው ዙር በተለያዩ ምክንያቶች ምደባ ያላገኙ ሰራተኞች በዩኒቨርሲቲው ምልመላና ምደባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 28 ላይ በተቀመጠው አማራጭ መፍትሄዎች መሰረት ጉዳያቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣቸዋል፡፡